# PATIENT RIGHTS AND RESPONSIBILITIES

የታካሚ መብቶች እና ኃላፊነቶች

**(Hospital - Revised May, 2022)**

( - 2022)

## PATIENT RIGHTS:

የታካሚ መብቶች፡-

As our patient, we have the responsibility to respect, protect, and promote your rights. You are a key member of your Health Care Team and you have the right to:

የኛ ታካሚ እንደመሆንዎ መብትዎን የማክበር፣የመጠበቅ እና የማሳወቅ ኃላፊነት አለብን፡፡ የጤና አገልግሎት የሚሰጥዎ ቡድን ቁልፍ አባል እንደመሆንዎ የሚከተሉት መብቶች አሉዎት፡፡

- Receive safe, quality care through the services that the hospital provides.
- ሆስፒታሉ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጥራት ያለው እንክብካቤን ያግኙ።
- Receive care and have visitation privileges without being discriminated against because of age, race, color, national origin, language, religion, culture, disability, sex, gender identity or expression, sexual orientation, or ability to pay.
- እድሜ፣ዘር፣የቆዳ ቀለም፣የመጡበት አገር፣ቋንቋ፣ ሀይማኖት፣ባህል፣የአካል ጉዳት፣ጾታ፣ የጾታ ለየት ያለ መግለጫ፣የጾታ አስተሳሰብ ወይም የመክፈል ችሎታ ሳይገድብዎ እንክብካቤና በሌሎች የመጎብኘት መብቶች ያግኙ።
- Choose who can and cannot visit you, without regard to legal relationship, race, color, national origin, religion, sex, sexual orientation, gender identity or disability. You may withdraw or deny consent for visitation at any time.
- ሕጋዊ ግንኙነት፣ዘር፣የቆዳ ቀለም፣የመጡበት አገር፣ ሀይማኖት፣ጾታ፣ የጾታ ለየት ያለ መግለጫ፣የጾታ አስተሳሰብ ወይም የአካል ጉዳት ሳይገድብዎ ማን እንዲጎበኝዎ ማን ደግሞ እንዳይመጣብዎ የመምረጥ መብት ይምረጡ። በማንኛውም ጊዜ ፈቃድዎን መከልከልና ስምምነትዎን መሰረዝ ይችላሉ፡፡
- Be informed when the hospital restricts your visitation rights for your health or safety, or the health or safety of patients, employees, physicians or visitors.
- ለደህንነትዎ ወይም ለጤናዎና ለሌሎች ህመምተኞች፣ሰራተኞች፣ሀኪሞችና ጎብኝዎች ደህንነት ወይም ጤና ሲባል ሆስፒታሉ ጉብኝት በሚከለከልበት ጊዜ ቀድሞ የማወቅ መብት፡፡
- Be informed of the hospital's policies about your rights and health care.
- ስለ ጤና አገልግሎቶችና ስለ መብቶችዎ ሆስፒታሉ ያለውን ፖሊሲ የማወቅ መብት፡፡
- Be treated with respect and dignity and be protected from abuse, neglect, exploitation and harassment.
- በአክብሮትና በሰብዓዊነት የመስተናገድና ከእንግልት፣ከንቀት፣ከብዝበዛ እና ከመዋረድ የመጠበቅ መብት፡፡
- Have your own physician and/or a family member, support person, or other individual be notified promptly of your admission to the hospital.
- ሆስፒታል ገብተው እንዲተኙ በሚወሰንበት ጊዜ ለቅርብ ሀኪምዎ፣ለቤተሰብ አባል፣ለሚያግዝዎ ሰው ወይም ለሌሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሰዎች በፍጥነት መረጃው እንዲደርስ ማድረግ፡፡

- Know the names and roles of hospital staff caring for you.
- እንክብካቤ የሚሰጡዎትን የሆስፒታሉ ባልደረቦች ስምና የሥራ ኃላፊነት ማወቅ፡፡
- Have a family member, support person, or other individual present with you for emotional support during the course of your stay, unless the individual's presence infringes on others' rights, safety, or is medically or therapeutically contraindicated.
- ሆስፒታል በሚቆዩበት ጊዜ አይዞዎት የሚልዎት የቤተሰብ አባል፣የሚረዳዎት ሰው ወይም ሌላ ሰው አብረዎት እንዲሆኑ የማድረግ መብት። የዚህ ሰው መኖር የሌሎችን መብት፣ደህንነት ወይም ከህመም የማገገም ሁኔታ የሚጋፋ እስካልሆነ ድረስ፡፡
- Have a family member, support person, or other individual involved in treatment decisions or make health care decisions for you, to the extent permitted by law.
- በሕግ እስከተፈቀደው ጥግ ድረስ ለእርስዎ በሚወሰኑ የህክምና አማራጮች ወይም አገልግሎቶች ላይ የቤተሰብ አባል፣ የሚረዳዎት ሰው፣ ወይም ሌሎች የሚመለከታቸው ሰዎች እንዲሳተፉ የማድረግ መብት፡፡
- Have an Advance Directive (health care directive, durable power of attorney for health care, or living will) that states your wishes and values for health care decisions when you cannot speak for yourself.
- ፍላጎትዎን በራስዎ አንደበት ማሳወቅ ባቃተዎ ጊዜ ለሚደረጉት የህክምና ውሳኔዎች ምኞቶችዎንና ፍላጎቶችዎን በጤና አገልግሎት መመሪያዎች፣ የጤና አገልግሎት የህግ ከለላ ስርዓት በኩል ወይም በኑዛዜ መልክ ማሳወቅ ይችላሉ፡፡
- Be informed about your health problems, treatment options, and likely or unanticipated outcomes so you can take part in developing, implementing and revising your plan of care and discharge planning. Discharge planning includes deciding about care options, choice of agencies or need to transfer to another facility.
- ስለ ጤናዎ እንክብካቤና ከሆስፒታል ሲወጡ ምን ማድረግ እንደሚኖርብዎ እቅድ በማውጣት፣በመተግበርና እቅድዎን በመመርመር እርስዎም ይሳተፉ ዘንድ የጤናዎ እክል ምን እንደሆነ፣ የህክምና አማራጮቹ ምን እንደሆኑ ከህክምናው የሚጠበቀው ወይም ይገኛል ተብሎ የሚታሰበው ውጤት ምን እንደሆነ የማወቅ መብት አለዎት። ከሆስፒታል ሲወጡ ከሚያስቧቸው ነገሮች መካከል የህክምና አማራጮችን መወሰን፣ክትትል የሚያደርጉበትን ቦታ የመምረጥ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ወደሌላ ተቋም መዛወር ይገኙበታል፡፡
- Have information about the outcome of your care, including unanticipated outcomes.
- የህክምና ሂደቱ ምን ውጤት እንደሚኖረው መረጃ ይኑርዎት፤ ይህ ያልታሰቡ የህክምናው ውጤቶችንም ይጨምራል፡፡
- Request, accept and/or refuse care, treatment or services as allowed by hospital policy and the law, and be informed of the medical consequences of your any refusal of care.
- በሆስፒታሉ ሕግና ደንብ መሰረት የሚሰጡ የተፈቀዱ የእንክብካቤ፣የህክምናና ሌሎች አገልግሎቶችን የመጠየቅ፣የመቀበል እና/ወይም የመቃወም እንዲሁም የትኛውንም ዓይነት ህክምና ሲቃወሙ ተቃውሞዎ በጤናዎ ላይ ስለሚያመጣው ውጤት መረጃ የማግኘት መብት አለዎት፡፡
- Ask for a change of care provider or a second opinion.
- ክትትል የሚያደርግልዎ ሰው እንዲቀየርልዎ ወይም ሁለተኛ አማራጭ እንዲሰጥዎ መጠየቅ ይችላሉ፡፡
- Have information provided to you in a manner that meets your needs and is tailored to your age, preferred language, and ability to understand.
- መረጃዎች ፍላጎትዎን፣ እድሜዎን፣የሚግባቡበትን ቋንቋ እና የመረዳት ችሎታዎን ባገናዘበ ሁኔታ እንዲሰጡዎት የመጠየቅ መብት አለዎት፡፡
- Have access to an interpreter and/or translation services to help you understand medical and financial information.

- መረጃዎች ፍላጎትዎን፣ እድሜዎን፣የሚግባቡበትን ቋንቋ እና የመረዳት ችሎታዎን ባገናዘበ ሁኔታ እንዲሰጡዎት የመጠየቅ መብት አለዎት፡፡
- Have your pain assessed and managed.
- የጤና እክልዎ ምን እንደሆነ የመመርመርና ህክምና የማግኘት መብት አለዎት፡፡
- Have privacy and confidentiality when you are receiving care.
- ህክምና በሚደረግልዎ ጊዜ ሚስጥርዎ እንዲጠበቅ የማድረግና ማንም ሌላ ሰው እንዳይገባብዎ የማድረግ መብት አለዎት፡፡
- Practice and seek advice about your cultural, spiritual and ethical beliefs, as long as this does not interfere with the well being of others.
- የሌሎችን ደህንነት የሚጋፋ እስካልሆነ ድረስ ባህላዊ፣ሀይማኖታዊ እና ሥነ-ምግባራዊ ልማዶችዎን ለማከናወን ምክር የመጠየቅና የመተግበር መብት አለዎት፡፡
- Request religious and spiritual services.
- ሀይማኖታዊና መንፈሳዊ አገልግሎቶችን የመጠየቅ መብት አለዎት፡፡
- Request a consult from the Ethics Committee to help you work through difficult decisions about your care.
- ስለ ጤና እንክብካቤዎ ውሳኔ ለመስጠት እጅግ አስቸጋሪ ሆኖ ካገኙት የሥነ-ምግባር ኮሚቴውን የምክር እገዛ ለመጠየቅ ይችላሉ፡፡
- Consent or refuse to take part in research studies as well as recordings, films or other images made for external use.
- ለተጨማሪ እውቀት ሲባል በሚካሄዱ የምርምር ጥናቶች፣ቀረጻዎች፣ፊልሞች ወይም ምስሎች በሚወሰዱባቸው ሥራዎች ለመሳተፍ ሊስማሙ ወይም ሊቃወሙ ይችላሉ፡፡
- Be free from restraints or seclusion, unless medically necessary or needed to keep you or others safe. If necessary, any form of restraint or seclusion will be performed in accordance with safety standards required by state and federal law.
- ለእርስዎ ወይም ለሌሎች ጤና አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ከማናቸውም ክልከላዎችዎና መገለሎች ነጻ የመሆን መብት አለዎት፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ማንኛውም የክልከላ ወይም የማግለል ድርጊት መፈጸም ያለበት በፌዴራልና በክልል የደህንነት መስፈርቶች አሰራር መሆን ይኖርበታል፡፡
- Have a safe environment, including zero tolerance for violence, and the right to use your clothes and personal items in a reasonably protected environment.
- ከኃይል ጥቃት ሙሉ በሙሉ ነጻ የሆነ፣ የግል ልብሶችዎንና የግል መገልገያ እቃዎችዎን በሚጠበቀው ደረጃ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ የመጠቀምና ደህንነቱ አስተማማኝ የሆነ አካባቢ የማግኘት መብት አለዎት፡፡
- Take part in decisions about restricting visitors, mail or phone calls.
- ጉብኝቶችን፣ የፖስታ መልእክትና የስልክ ጥሪዎችን በመገደብ ውሳኔ ውስጥ የመካፈል መብት አለዎት፡፡
- Receive protective oversight while a patient in the hospital, and receive a list of patient advocacy services (such as protective services, guardianship, etc.)
- በሆስፒታል ታካሚ ሆነው እስከቆዩ ድረስ በየጊዜው የደህንነትዎን መጠበቅ የመታየትና የታካሚ መብቶች አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላሉ፡፡ (ለምሳሌ የክትትል አገልግሎቶች፣ የጥበቃ አገልግሎቶች የመሳሰሉት)
- Receive compassionate care at the end of life.
- የህይወትዎ ማብቂያ ላይ በደረሱበት ወቅት ርህራሄ የተሞላው እንክብካቤ የማግኘት መብት አለዎት፡፡

- Donate, request or refuse organ and tissue donations.
- የሰውነትዎን አካል እና ሕዋስ ለመለገስ ወይም ላለመለገስ እንዲሁም እንዲሰጥዎ የመጠየቅ መብት አለዎት፡፡
- Review your medical record and receive answers to questions you may have about it. You may request amendments to your record and may obtain copies at a fair cost in a reasonable time frame.
- የህክምና ማህደርዎን የመመርመርና ለሚኖርዎት ጥያቄዎች በሙሉ መልስ የማግኘት መብት አለዎት፡፡ ማህደርዎ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ የማህደርዎን ቅጂ ከፈለጉም በተመጣጣኝ ዋጋና ጊዜ በማይፈጅ ሁኔታ የማግኘት መብት አለዎት፡፡
- Have your records kept confidential; they will only be shared with your caregivers and those who can legally see them. You may request information on who has received your record.
- ማህደርዎ በምሥጢር እንዲጠበቅና ማየት የሚችሉት እንክብካቤ የሚሰጡዎት ሰዎችና ሌሎች ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው ሰዎች ብቻ እንዲሆኑ ማድረግ ይችላሉ፡፡ የህክምና ማህደርዎን ማን እንዳየው መረጃ መጠየቅ ይችላሉ፡፡
- Receive a copy of and details about your bill.
- ስለ ህክምና ወጪዎ ዝርዝር መረጃና የወጪውን ዝርዝር ቅጂ ማግኘት ይችላሉ፡፡
- Ask about and be informed of business relationships among payors, hospitals, educational institutions, and other health care providers that may affect your care.
- በህክምናዎ ላይ ተጽእኖ ሊያመጡ ስለሚችሉ በከፋዮች፣በሆስፒታሎች፣በትምህርት ተቋማት እና በሌሎች የጤና አገልግሎት ሰጪዎች መካከል ስላለው የሥራ ግንኙነት፣ መረጃ መጠየቅና ማግኘት ይችላሉ፡፡
- Know the hospital’s grievance process and share a concern or grievance about your care either verbally or in writing and receive a timely written notice of the resolution. If you have a grievance or concern, please contact (Enter entity-specific instructions, including number) at ___________. You may also contact:
- ሆስፒታሉ ቅሬታዎችን የሚያስተናግድበትን ሂደት ማወቅና ስለ ህክምናዎ የከነከንዎት ነገር ወይም የሚያቀርቡት ቅሬታ ካለ በቃል ወይም በጽሁፍ ማቅረብና ወቅቱን የጠበቀ ምላሽ ወይም መፍትሔ በጽሑፍ የመቀበል መብት አለዎት፡፡ የከነከንዎት ነገር ወይም ቅሬታ ካለዎት የተገልጋይ ቅሬታ ቢሮን በ ____________ ደውለው ያነጋግሩ፡፡ እንዲሁም ማነጋገር ይችላሉ፡ -

  Missouri Department of Health & Senior Services
  Health Services Regulation
  P.O. Box 570
  Jefferson City, MO 65102-0570
  Phone: 1-573-751-6303

  ሚዙሪ የጤና መምሪያ እና ሲኒየር አገልግሎቶች
  የጤና አገልግሎት ደንብ
  ፖ.ሳ.ቁ 570
  Jefferson City, MO 65102-0570
  ስልክ: 1-573-751-6303

  The Joint Commission
  Office of Quality Monitoring
  One Renaissance Boulevard

Oakbrook Terrace, IL 60181
Email: complaint@jointcommission.org
Fax: 1-630-792-5636
Complaint Line: 1-800-994-6610

The Joint Commission
Office of Quality Monitoring
One Renaissance Boulevard
Oakbrook Terrace, IL 60181
ኢ-ሜል: complaint@jointcommission.org
ፋክስ፡ 1-630-792-5636
የቅሬታ መስመር፡ 1-800-994-6610

Livanta LLC
BFCC-QIO Program, Region 7
10820 Guilford Rd, Suite 202
Annapolis, Junction, MD 20701-1105
Phone: 1-800-634-4557, Ext. 2470

Livanta LLC
BFCC-QIO Program, Region 7
10820 Guilford Rd, Suite 202
Annapolis, Junction, MD 20701-1105
ስልክ: 1-800-634-4557፣ Ext. 2470

## PATIENT RESPONSIBILITIES

**የታካሚ ኃላፊነቶች**

You and/or your family member, support person, or other designated individual acting on your behalf have the responsibility to:

እርስዎ ወይም የቤተሰብ አባል፣የሚግያዝዎ ሰው ወይም እርስዎን ወክሎ እንዲናገር በሕግ ስልጣን የተሰጠው ሰው የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉበት፡፡

- Provide correct and complete information about yourself and your health, including present complaints, past health problems and hospital visits, medications you have taken and are taking (including prescriptions, over-the-counter and herbal medicines), and any other information you think your caregivers need to know.
- ስለ እርስዎና ስለጤና ሁኔታዎ ትክክለኛና የተሟላ መረጃ የመስጠት ማለትም አሁን ያለዎትን የጤና እክል፣ ከዚህ ቀደም ያጋጠመዎን የጤና ችግርና ሆስፒታል የሄዱባቸውን ጊዜያት፣ወስደዋቸው የነበሩ ወይም አሁን እየወሰዷቸው ያሉ መድኃኒቶች (የታዘዘልዎን መድኃኒት፣ያለሀኪም ትእዛዝ የሚወስዷቸውንና ሌሎች የቅጠላቅጠል መድኃኒቶች ጨምሮ) እና እንክብካቤ ለማድረግ የተዘጋጁትን ሰዎች ይጠቅማል የሚሉትን ማንኛውንም መረጃ የማካፈል ኃላፊነት ይኖርብዎታል፡፡
- Follow your agreed-upon care plan and report any unexpected changes in your condition to your doctor.
- ከሀኪምዎ ጋር የተስማሙበትን የህክምና እቅድ መከተልና ያልተጠበቀ ለውጥ ወይም ሁኔታ ካዩ ለሀኪምዎ የማሳወቅ ኃላፊነት አለብዎ፡፡

- Ask questions when you do not understand your care, treatment, and services or what you are expected to do. Express any concerns about your ability to follow your proposed care plan or course of care, treatment, and services.
- ስለእንክብካቤው፣ህክምናው እና የጤና አገልግሎቶች ያልገባዎ ነገር ካለ ወይም ከእርስዎ ምን እንደሚጠበቅ ካልተረዱ ጥያቄዎችን የመጠየቅ ኃላፊነት አለብዎ። የተሰጥዎትን የእንክብካቤ እቅድ፣ህክምናውን እና የጤና አገልግሎቶችን ለመከታተል ስላለዎት ችሎታ ሀሳብ ከገባዎ ይህንን የማሳወቅ ኃላፊነት አለብዎ።
- Accept consequences for the outcomes if you do not follow the care, treatment, and service plan.
- በታቀደልዎ የእንክብካቤ፣የህክምናና የአገልግሎት ሥርዓት መሰረት ባለመሄድዎ የሚመጣውን ውጤት የመቀበል ኃላፊነት አለብዎ።
- Speak up and share your views about your care or service needs and expectations, including your pain needs and any perceived risk or safety issues.
- ስለ እንክብካቤዎና ስለሚሰጥዎት አገልግሎት ፍላጎቶችዎ እና እንዲሆንልዎ ስለሚፈልጉት ነገር እንዲሁም ለህመሜ ያስፈልገኛል ወይም ለደህንነቴ ያሰጋኛል ስለሚሏቸው ነገሮች በግልጽ መናገርና ሀሳብዎን የመግለጽ ኃላፊነት አለብዎ።
- Provide correct and complete information about your Advance Directive if you have one and provide a current copy.
- የአድቫንስ ዳይሬክቲቭ ካለዎት ወቅታዊ ቅጂ ማቅረብና ትክክለኛና የተሟላ መረጃ የመስጠት ኃላፊነት አለብዎ።
- Respect the rights, property, privacy, dignity, and confidentiality of patients and others in the hospital.
- በሆስፒታሉ የሚታከሙና የሌሎች ሰዎችን መብት፣ንብረት፣ነጻ የመሆን መብት፣ክብር እና ምስጢር የማክበር ኃላፊነት አለብዎ።
- Be respectful in your interactions with other patients, employees, physicians and visitors without regard to age, race, color, national origin, language, religion, culture, disability, socioeconomic status, sex, gender identity or expression, or sexual orientation.
- ከሌሎች ታካሚዎች፣ ሰራተኞች፣ሀኪሞችና ጠያቂዎች ጋር የሚኖርዎ ግንኙነት እድሜ፣ዘር፣የቆዳ ቀለም፣የመጡበት አገር፣ ቋንቋ፣ሀይማኖት፣ባህል፣የአካል ጉዳት፣የኢኮኖሚ ደረጃ፣ጾታ፣የጾታ ልዩ መገለጫ፣ ወይም የጾታ አመለካከት ሳይለይ አክብሮት የተሞላበት መሆን ይኖርበታል።
- Follow instructions, hospital policies, rules and regulations which include respecting property and helping control noise.
- የሆስፒታል መመሪያዎችን፣ ንብረት ማክበርና ድምጽ መቀነስን የመሳሰሉ ህጎችና ደንቦችን በመመሪያው መሰረት መከተል ይኖርብዎታል።
- Leave your valuables and personal belongings at home, have your family members take them home, or have them placed with Security until you are discharged.
- የግል እቃዎችዎንና ዋጋ ያላቸውን ንብረቶችዎን ቤት ትተው መምጣት ወይ የቤተሰብ አባል ወደቤት እንዲወስዳቸው ማድረግ ካልሆነ ደግሞ ከሆስፒታል እስኪወጡ ድረስ በሆስፒታሉ ማቆያ በአደራ እንዲቀመጥልዎ ማድረግ አለብዎት።
- Keep our environment tobacco-free. You may not use any tobacco products while inside or outside this health care facility.
- አካባያችን ከሲጋራ ጭስ የጸዳ እንዲሆን የማድረግ ኃላፊነት አለብዎት። በዚህ የህክምና ተቋም ተገልጋይ ሆነው እስቆዩ ድረስ በግቢው ውስጥም ሆነ ውጪ ማንኛውንም ዓይነት የትምባሆ ምርቶች መጠቀም አይችሉም።

- Keep a safe environment free of drugs, alcohol, weapons, and violence of any kind, including verbal intimidation.
- ከአደንዛዥ እጽ፣ አልኮል መጠጥ፣ መሳሪያዎች እና በቃላት ማስፈራራትን ጨምሮ ከማንኛውም ዓይነት የኃይል ጥቃቶች የጸዳ አካባቢ እንዲኖር ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- Provide correct and complete information about your financial status as best you can and promptly meet any financial obligations to the hospital.
- ስለ ገንዘብ አቅምዎ የሚችሉትን ያህል ትክክለኛና የተሟላ መረጃ የመስጠትና ለሆስፒታሉ መክፈል ያለብዎ ማንኛውም ገንዘብ ነክ ግዴታዎች ካሉብዎ በአፋጣኝ ክፍያ የመፈጸም ኃላፊነት አለብዎት፡፡
- For more information about your Patient Rights and Responsibilities, please call (Entity information)
- ስለ ታካሚ መብቶችዎ እና ኃላፊነቶችዎ የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ይደውሉ (የህጋዊ አካል መረጃን)